ልክ እንደ 1፣ 2፣ 3 ቀላል ነው!

# የጤና እቅድዎን መጠቀም

## 1 የመጀመሪያ ክፍያዎን መክፈል

**ከእርስዎ ኢንሹራንስ ኩባንያ የተገኘ መረጃ።** የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎ ስለ እቅድዎ እና ወርሃዊ ክፍያዎ (ፕሪሚየም) እንዴት እንደሚከፍሉ በፖስታ ወይም በኢሜል መረጃን ይልክልዎታል።



**የመጀመሪያ ክፍያ።** የመጀመሪያ ክፍያዎን ወዲያውኑ መክፈል አስፈላጊ ነው፣ እቅድዎ በሚጀምርበት ወር መጀመሪያ ላይ።

**ሂሳብ ካልተቀበሉ ለመክፈል ወደ ኢንሹራንስ ኩባንያዎ ይደውሉ።** የኢንሹራንስ ኩባንያው የመጀመሪያ ክፍያዎን ሙሉ በሙሉ እስኪቀበል ድረስ ሽፋንዎ አይጀምርም። ክፍያዎችን የሚፈፅሙት ዘግይተው ከሆነ የኢንሹራንስ ኩባንያዎ እቅድዎን ሊሰርዘው ይችላል።

**ስለ ሂሳብዎ ወይም ሽፋንዎ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ በቀጥታ የኢንሹራንስ ኩባንያዎን ያነጋግሩ፡-**

- CareFirst፡- **855-444-3121፤ member.carefirst.com**
- Kaiser Permanente፡- **844-524-7370፤ kp.org/paypremium**
- UnitedHealthcare፡- **1-800-691-0021፤ myuhc.com/exchange**
- Aetna Health፡- **844-365-7373 (TTY፡- 711)፤ AetnaCVSHealth.com/payment**

**የአባል መታወቂያ ካርድ።** ሂሳብዎን ከከፈሉ በኋላ የኢንሹራንስ ኩባንያዎ የአባል መታወቂያ ካርድ በፖስታ ይልክልዎታል። ምንም እንኳን ካርድ ያልተቀበሉ ቢሆንም፣ ሒሳቡ አንዴ ከተከፈለ የጤና አገልግሎቶችን መጠቀም ይችላሉ።

## 2 የእርስዎን ሽፋን እና ወጪዎች መረዳት

**የትኞቹ አገልግሎቶች ይሸፈናሉ?** ሁሉም የግል የጤና ዕቅዶች እንደ እነዚህ ዋና ጥቅሞች እና ሌሎችን መስጠት አለባቸው፡-

- በሃኪም መታየት
- ሆስፒታል መተኛት
- የድንገተኛ ህክምና እንክብካቤ
- በሐኪም የታዘዙ
- የአእምሮ ጤና እንክብካቤ
- የወሊድ እና አዲስ የተወለዱ ህፃናት እንክብካቤ
- የሕፃናት ሕክምና

እንደ ክትባቶች፣ ጤንነትን መታየት እና ምርመራዎች ያሉ የመከላከያ እንክብካቤዎች እንዲሁ ምንም ወጪ እርስዎን ሳያስወጣዎት ይሸፈናል፣ ምንም እንኳን ዓመታዊ ቅድመ ክፍያዎን ባይተገብሩም። መሸፈን ያለባቸውን ሁሉንም አገልግሎቶች ለማየት **MarylandHealthConnection.gov/choose-a-plan** ን ይጎብኙ።


© 2023 Maryland Health Benefit Exchange | MHC018_102023_AM

# የጤና እቅድዎን መጠቀም

**የእርስዎ የተለየ ዕቅድ ምን እንደሚሸፍን ይወቁ።** የኢንሹራንስ ኩባንያዎን ድረ-ገጽ ይጎብኙ ወይም እቅድዎ ስለሚሸፍነው በፖስታ የተላከለዎትን ማንኛውንም መረጃ ይመልከቱ። ጥያቄዎች ካሉዎት በቀጥታ ወደ ኢንሹራንስዎ ይደውሉ።

**የእቅድ ወጪዎችን እና ቁልፍ ቃላትን ይረዱ።** ለአገልግሎቶች ምን ያህል እንደሚከፍሉ ተፅኖ ሊኖራቸው የሚችሉ አንዳንድ የተለመዱ ቃላቶች እዚህ አሉ:-

- **ዓመታዊ ቅድመ ክፍያ:-** የጤና ኢንሹራንስዎ ወይም እቅድዎ መክፈል ከመጀመሩ በፊት እቅድዎ የሚሸፍነው ለጤና እንክብካቤ አገልግሎት ያለበዎት ዕዳ መጠን።
- **ኮኢንሹራንስ:-** ከተሸፈነው የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ወጪዎች የእርስዎ ድርሻ፣ ለአገልግሎቱ ከተፈቀደው መጠን በመቶኛ (ለምሳሌ:- 20%) ይሰላል።
- **ትስስር:-** በእቅድ ውስጥ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት የተስማሙት ሀኪሞች፣ ሌሎች የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች እና ሆስፒታሎች።
- **ኮፔይመንት (ኮፔይ):-** የተወሰነ መጠን (ለምሳሌ $15) ለተሸፈነ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ይከፍላሉ፣ አብዛኛውን ግዜ አገልግሎቱን ሲቀበሉ።

## 3 አቅራቢን መፈለግ እና የእርስዎን ኢንሹራንስ መጠቀም



**በእቅድዎ ውስጥ ያለ ሐኪም ይፈልጉ።** በእቅድዎ ትስስር ውስጥ የሚገኙ ዶክተር ወይም አገልግሎት አቅራቢን ሲያዩ ለአገልግሎቶች ዝቅተኛ ወጪዎችን ይከፍላሉ። እቅድዎን የሚቀበል ዶክተር ለማግኘት:-

- ወደ ኢንሹራንስ ኩባንያዎ ይደውሉ ወይም በድር ገፁ ላይ ይመልከቱ።
- በ ኦንላይን **MarylandHealthConnection.gov/find-a-provider** ኦንላይን ላይ ይፈልጉ።
- እሱ ወይም እሷ ኢንሹራንስዎን ይቀበሉ እንደሆነ ለመጠየቅ ወደ ዶክተርዎ ቢሮ ይደውሉ።

**ለመጀመሪያ ቀጠሮዎ ይዘጋጁ።** አገልግሎት አቅራቢ ካገኙ እና የመጀመሪያ ቀጠሮዎን ካስያዙ በኋላ፣ እነዚህን ቀጠሮዎ ላይ ይዘው ይምጡ:-

- የኢንሹራንስ ካርድዎ
- በአሁኑ ጊዜ የሚወስዷቸው የማንኛውም መድሃኒቶች ዝርዝር
- የኮፔይ ክፍያ፣ የሚኖርዎት ከሆነ

**ከመታመምዎ በፊት፣ የሚፈልጉትን ህክምና እንክብካቤ ያግኙ።** በ Maryland Health Connection በኩል የሚሸጡ ሁሉም ዕቅዶች የመከላከያ ህክምና እንክብካቤ እና ሥር ሰደድ በሽታ አያያዝን በነፃ ይሸፍናሉ፣ በእቅድዎ ትስስር ውስጥ የሚገኝ ዶክተር እስካዩ ድረስ። ብዙ ጤንነትን መታየትወይም ቼካፕ፣ ክትባቶች እና ምርመራዎች ምንም ወጪ እርስዎን ሳያስወጣዎት ይሸፈናል:-

- የጉንፋን እና የሳንባ ምች ክትባቶች
- የወሊድ መቆጣጠሪያ
- መደበኛ ክትባቶች
- ሙሉ የሴቶች ምርመራ
- የአእምሮ ጤና ምርመራ እና የምክር አገልግሎት
- እንደ የደም ግፊት፣ የስኳር በሽታ፣ ማሞግራምና ኮሎንስኮፒ የመሳሰሉ የካንሰር ምርመራዎች
- የቤት ውስጥ ጥቃት ምርመራ እና የምክር አገልግሎት



© 2023 Maryland Health Benefit Exchange | MHC018_102023_AM